# 5ኛው ዓመት የሰማዕታት ቀን
# በአሲምባ የውይይት መድረክ

**ቅዳሜ ነሐሴ 29 ቀን 2002 ዓ.ም**

የአሲምባ የውይይት መድረክ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለሀገራቸው ባላቸው ፍቅር፤ የጥቂቶች መጫወቻ የነበረችውን ኢትዮጵያ የብዙሃኑ ለማድረግ፤ ሕዝባችንን ከዘመናት የመከራ ማቅ ለአንዴም ለሁሌም ለማላቀቅ፤ የስልጣን ሱስ ካሰከራቸው የሀገር ሀፍረቶች፤ ፋሺሽቶችና ጠባብ ብሔረተኞች ጋር ተናንቀው ሕወታቸውን በድፍረት መስዋዕትነት ለከፈሉ፤ ሕይወታቸውን ሰጥተው ሕይወት ለሰጡን፤ የጀመሩት ዕውነተኛ የሕዝባዊ ሥርዓት ምሥረታ ትግል ባግባቡ እንዲቋጭ፤ በአደራም የተቀበልነውና ለሌላም ትውልድ የማንለጋው ኃላፊነት እንደሆነ በመገንዘብ፤ እኛም ከመቼውም የበለጠ ለመታገል ቃላችንን መልሰን የምናድስበት፣ ታግለው ላታገሉን ለኒያ የቁርጥዬ ቀን የኢትዮጵያ ጀግኖች ታሪካቸውን በቅርብ ከሚያውቋቸው የምንሰማበት፣ እነሱንም በማሰብ፤ አደራ በላዎች አለመሆናችንን የምናረጋግጥበትና የምናመሰግናቸው ዕለት እንዲሆን ለ5ተኛ ጊዜ ይህን የሰማዕታት ቀን በመድረካችን አክብረን ስለምንውል ሀገር ወዳድ ወኖቻችን በሙሉ የዚህ ዝግጅት ተካፋይ እንድትሆኑ ተጋብዛችኋል።

በዕለቱ የተለያዩ የክብር እንግዶች ይኖሩናል።

በዚህ የሰማዕታት ቀን ለመሳተፍ የምትሹ ሁሉ በዚያን ወቅት ያለፉ ወገኖችን የምታስታውሱበት ዕድል በመሆኑ በዚያ ጨለማ የቂይ ሽብር ወቅት የምታውቁትን ወኝ ታሪክ ይዛችሁልን እንድትመጡ እናሳስባለን።

የአሲምባ ውይይት መድረክ